# ያልጣዱት አይበስልም

(በእውቀቱ ስዩም)

ፍቅር እንደ ዝናብ ከሰማይ አይወርድም
ያበባ መደብ ነው
በሰው የሚታነፅ ፡ በሰው የሚወድም
ተዘርቶብን እንጂ ፡ተሰብከን አንወድም፡፡

"ወዳጄ ወዳጄ " የሚያቀነቅኑ
አገር ያቀኑ ለት መች ልብን አቀኑ

ሳይወጡ ሳይወርዱ
ውብ ስራን ከውብ ቃል ፡ሳያስተባብሩ
ከድሜ እና ከምኞት ቆርሰው ሳይገብሩ
ፍቅር መች ይፈልቃል?
በስብከት በምልጃ በየዋህ ሰዎች ህልም
ያልጣዱት አይበስልም
ያልዘሩት አይበቅልም፡፡